# አንጋፋው ደራሲ አዳም ረታ

ሰለሞን አበበ ቸኮል

አዲስ አድማስ፤ ሐምሌ 2008

‹‹የስንብት ቀለማት ያለቀ ሳይሆን ያረፈ-----ሆኖ ነው የሚሰማኝ››

በተለየ የአጻጻፍ ዘይቤውና በጭብጥ አመራረጡ እንዲሁም በውብ የቋንቋ አጠቃቀሙ የበርካታ አንባቢያንን ቀልብ መግዛት የቻለው አንጋፋው የልብወለድ ደራሲ አዳም ረታ፤በኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ታሪክ አዳዲስ ሪከርዶችን (አውቆም ይሁን ሳያውቅ) ማስመዝገቡን ቀጥሏል፡፡ ኑሮውን በቋሚነት ባህር ማዶ ቢያደርግም ቅሉ ባለፉት ስምንት ዓመታት ስምንት መጽሐፍትን ለአንባቢያኑ ከማድረስ አላገደውም-- -በዓመት አንድ መጽሐፍ እንደማለት ነው፡፡ በቅርቡ ለንባብ ያበቃው አዲሱ የረዥም ልብወለድ መጽሐፉ፤በትልቅነቱ (በገጾች ብዛት) እንኳን በኢትዮጵያ በአፍሪካም የሚወዳደረው የለም፡፡

በ960 ገጾች የተቀነበበው የስንብት ቀለማት፤በዋጋም አዲስ ክብረወሰን ያስመዘገበ ይመስላል፡፡ የትኛውም የአማርኛ ልብወለድ መጽሐፍ በ350 ብር የተሸጠበት ጊዜ የለም፡፡ የፈጠራ ሥራዎቹን ከሸኖ ከማቅረብ ውጭ እምብዛም ሚዲያ የማያዘወትረው አዳም ረታ፤አዲስ መጽሐፍ ባወጣ ማግስት ቃለምልልስ ሲሰጥ የአሁኑ የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ጋዜጠኛ ሰሎሞን አበበ ቸኮል በአዲሱ ልቦለዱ የስንብት ቀለማት ዙሪያ ከደራሲ አዳም ረታ ጋር ሰፊ ቃለ-ምልልስ አድርጓል፡፡ እነሆ፡-

የአዲሱን መጽሐፍህን ርዕስ ለምን "ስንብት" አልከው?

ስንብት ብቻውን አይሆንም፡፡ ቀለማት መጨመር አለበት፡፡ ስም ከነአባቱ እንደ ማለት ነው፡፡ ከገርያቱ የሚሰናበቱት ከነበሩበት፣እንደ ደንብ ቢመቻቸውም ባይመቻቸውም፣ ቢፈልጉትም ባይፈልጉትም፣ ጥፉትም ይሁን ልማት፣ ወደውም ይሁን ሳይወዱ ወደ ሌላ ደንብ ሲሸጋገሩ ይገኛሉ፡፡ ይሄም ሽግግር የተለያየ ነው፡፡ የተለያየ ቀለም አለው፡፡ ይሄ ፍፁም ስንብትን ወይም ሞትን ይጨምራል፡፡

እንደተለመደው፤ ርዕሱ ውስጥ በቀጥታ ጠቅሰኸዋል። ነድ የተባለው የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ በሕዳግ ማስታወሻ ይሄ ስያሜ ይነሳል፡፡ ዮሐንስ ወላይሶ የተባለ የባህል ሐያሲ ከአንድ ጋዜጠኛ በቀረበለት ቃለ መጠይቅ አርዕስቱን ይጠቅሰዋል፡፡ ዮሐንስ ለከፍተኛ ትምህርት አሜሪካን በነበረበት ወቅት መጻፍ የጀመረውና ከግብ ያልደረሰለት ልብወለዱ ስያሜ ነው፡፡ እሱ በእንግሊዘኛ ዘ ከለርስ ኦፍ አዲዮስ ብሎ የሰየመውን ወደ አማርኛ በመመለስ ለማዛመድ ተሞክሮአል፡፡ በትርጉም ደረጃ ይሄን ድርሰት ከዮሐንስ ልብወለድ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ እሱ ከሰጠን መረጃ ከጀመረው ልቦለዱ፣ እዚህ የገቡት ብዙ ብዙ የምትባል እና አንተ ጎዳና አንተ መንገድ የተባሉት ምዕራፎች ብቻ ናቸው፡፡ ዮሐንስ በእንዝህላልነት ያላጠናቀቀውን ነገር ወደ ዛሬ በማምጣት፣አሚሚቱ ወይም ስንብቱ እንዳይጠቁር በማስታወስ ጎዳና እርቅ የመፍጠር ነው፡፡ በሌላ ሰው አፍ ዮሐንስን ለመዘከር ነው፡፡ መሞቱን የምናውቀው ግን ነጭ የተባለው ስምንተኛው ክፍል ውስጥ ነው፡፡ በነጭናጫ ሐያሲነቱ ሰላም የነሳቸው ካሉ፣ መጨረሻ ላይ መሞቱን ሲሰሙ ተገላገልን እንደማይሉ እጠረጥራለሁ፡፡

ገና ስትጀምር ረዥም ልብወለድ እጽፋለሁ ብለህ አስበህ ነበር?

ብዙ ጊዜ በቢጋር አልሰራም፡፡ አይመጣልኝም፡፡

እንደመጣልኝ እጀምራለሁ፡፡ ቀስ በቀስ ያብጣል (በተሳሳተ መንገድ) ወይ ያድጋል (በትክክል)፡፡ ለምሳሌ ገባኅርያቱን የመለመልኩት በእጣ ነው፡፡ 27 የሚደርሱ ባኅርያትን (ስንዝሮን ሳይጨምር) በትናንሽ ወረቀት ላይ ስማቸውን ፌ፣ ወረቀቶቹን ጠቅልዬ፣ ሰሃን ውስጥ አስገብቼ እንደ ዕጣ በመልቀም ነው፡፡ ይሄን የምነግርህ ምን ያህል እቅድ እንዳሌለኝ እንድታይ ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ አልቋል ብዬ የተውኩት የስንብት ቀለማት የዚህን አንድ ሶስተኛ አያክልም ነበር፡፡ ያለቀ የሚመስለው ድርሰት አለማለቁን የምትገነዘበው፣አለቀ ያልካቸውን ምዕራፎች ጎን ለጎን አስቀምጠህ ስታያቸው ነው፡፡ ከጀርባ ያልጠበቅኸው አይነት ግንኙነት እንዳላቸው ትረዳለህ፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ ለመለወጥ ይቁነጠነጣል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ ሞተር (ፊክሽናል ጄኔረተር) ይሆናል፡፡ ቀስ ብሎ የሚከሰት የኮንሴፕት መስክ (ኮንሴፕት ፊልድ) ወይም የፎርም መስክ (ፎርም ፊልድ) ያጋጥምሃል፡፡ ይሄ በመፃፍ ዲዛየር ወይም ምኞት ይሞላሃል፡፡ እናም ይሄ ግንኙነት ከጨረስካቸው ምዕራፎች አልፎ ወደ ውጭ በየቦታው ይፈሳል፡፡ ውጭ ማለት በቅድሚያ ድርሰቱ ይሄዳል ብለህ ወደአላሰብክበት እንግዳ አካባቢ ማለት ነው፡፡ ተጠናቋል

ካልካቸው ምዕራፎች ገፀባህርያት፣ ጊዜ፣ ገጠመኝ፣ ድባብ፣ ልዋጭ በመንጠቅ ሌሎች ታሪኮች ትገነባለህ፡፡ ወይም ሌሎች ምዕራፎች ይገነባሉ፡፡ አገነባቡ ግን እንደ ድር ነው፡፡ ከቀናህ ማድራት ይሆናል፡፡ ይሄ ልፋትህ አንድ ደረጃ ሲደርስ ይቁነጠነጡ የነበሩት ምዕራፎች ሲረጋጉ ይሰማሃል፡፡ እንዲህ ሲሆን አልቋል ከማለት አርፈዋል ማለት ይሻላል፡፡ የስንብት ቀለማት ያለቀ ሳይሆን ያረፈ፣ ጊዜ ጠብቆ ለጉዞ የሚነሳ ሆኖ ነው የሚሰማኝ፡፡ ትዕግስት ጊዜውና ችሎታው ካለ፤ ይሄን 960 ገጽ በተለያየ አቅጣጫ መወጠርና ማስፋት ይቻላል፡፡ በሰፋ ቁጥር እምቅ ሃይሉ እየበረታ ይሄዳል፡፡ ምክንያቱም አዲስ ቁስ ያግበሰብሳል፡፡ በዚህ ሂደት የተገነዘብኩት ነገር፣ በዝርዝር ንድፍ መስራት እንደሚበጅ ነው፡፡ ዳይናሚክ ሂደቱና ሕልውናው ነፃነትን ለብሶ ቁጥጥርን ይጋርዳል፣ በሆነ መልክ ከውጭ የሚፀነስ ግብታዊነት በአንተ ላይ (ደራሲው ማለት ነው) ሃያል ይሆናል፡፡

እና፣ ራሱ ረዘመ እንጂ መርዘሙን ልብ አላልኩም፡፡ እንዲህ ስልህ ግራ ሊገባህ ይችላል፣ እያየኸው! ልትለኝ ትችላለህ፡፡ ካለው እምቅ (ፖቴንሽያል) ሃይል አንፃር አልረዘመም፡፡ ግን መርዘሙንና አለመርዘሙን የምንለካው በገፁ ብዛት ሳይሆን አሁን በእረፍት ላይ ያለው የስንብት ቀለማት ንጥረ-ነገሮቹ ወይም ታሪኮቹ እምቅ ሃይል አላቸው? ይሄንንስ ወደ ድርጊት ለመለወጥ የሚያስችል ተስፋ ይሰጣሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች መልሼ ነው፡፡ ሕናዊነት የሚጠይቅህ መጀመሪያ ዘሩን የመዝራት ነው፡፡ ዘሩ ከአንድ በላይ ያለቀ ወይም ያላለቀ ታሪኮች ናቸው፡፡ ከዚህ በሁዋላ እነዚህ ራሳቸው ሌላ ዘር ይሰጣሉ ይራባሉ፤ፊክሽናል ጀኔረተረስ እንዳልኩህ፡፡ በትክክል አዳጋች ይሆናሉ፡፡ አዳጋችነትን መቀበል ደንብ ነው፡፡ ደሞስ 960 ገን ረዘመ የሚለው ማነው? ማለት ከምን ከማን አወዳድረን? እንደውም ካለው እምቅ ሃይል ተነስቼ ያንሰዋል ልል እችላለሁ፡፡ ለአንባቢ መድረሱ እንጂ ወሰኑ፣ ሌላ ወሰን የለውም፡፡ የሳንቲም ዋጋው እንጂ ምናቡ አይደለም፡፡

አንዳንዶቻችን መጽሐፉን ሳናይ፣የረዘመበት ታሪክ ጨምሮበት ይሆናል ብለን አስበን ነበር---

ብዙ ታሪክ የለውም፡፡ ምናብና ማህበራዊ ታሪክ ግራና ቀኝ ተቀምጠው፣ተነጣጥለው የምናያቸው ነገሮች አይደሉም፡፡ ታሪካዊ ሁኔታ ወስጥ ልብወለድ፣ በልብወለድ ሁኔታ ውስጥ ታሪክ አስገባለሁ፡፡ ይሄ ብወዛ ታሪኩን ከልብወለዱ ነጥሎ ማውጣት አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ነጥዬ ላውጣ ካልክ ለአንዱ አዳልተህ ነው፡፡ ግን እሱንም ታሪክ ነው ብለህ እንደ ዋቤ መጠቀም ችግር አለው፡፡ ምክንያቱም የሆነ ጎኑ በልብወለድ ተከልሷል፡፡

መጽሐፉን ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ፈጀብህ ?

ስጽፍ አንድ መጽሐፍ ላይ ብቻ አላተኩርም፡፡ ስለዚህ የአንዱን መጽሐፍ ሕይወት ነጥዬ ጊዜውን ማስላት ይከብደኛል፡፡ የስንብት ቀለማትን እየሰራሁ፣ የ600 ገጹ መረቅ ልብወለድ ከመሃል ገብቷል፡፡ ስገምት ምናልባት አራት አመት ወስዷል፡፡ ካነሰብህ ትንሽ ጨምርበት፡፡ ከበዛብህም ትንሽ ቀንስለት፡፡ ግድየለኝም፡፡

ቁጭ ብለህ ይህን ያህል ስትጽፍ፣… አይታክትህም?

ብዙ ጊዜ ሰዎች መጻፍን ከመቀመጥ ጋር፤ ከዛ መቀመጥን ከማረፍ ጋር፤ ማረፍን ደሞ ፣ያለምንም እፍረተ-ቢስነት፣ ከስንፍና ጋር ሊያይዙት ይችላሉ፡፡ በዚህ የትርጉም ሂደት መፃፍ መነሻ መሆኗ ይረሳል፣ ባይረሳም አድካሚነቷ ከአእምሮ ስራ ጋር ብቻ የተያያዘ ይሆናል፡፡ ምናልባትም ከአእምሮ መባዘን ጋር፡፡ ብዙ ሰዎች መፃፍ አካል አድካሚ እንደሆነ አይረዱም፡፡ እግርህ ድረስ ይደክምሃል፡፡ የአንገት ጣመኑ ከባድ ነው፡፡ እንደ ስንብት ቀለማት ደሞ ራሱን የቻለ ሎጂስቲክ የሚያስፈልገው ልብወለድ አለ፡፡ የምታነበውን ማቴሪያል ተዟዙረህ ማግኘት፣ ማስታወሻ መውሰድ አለብህ፡፡ አንዳንዴ አስር ገ ማስታወሻ ሰርተህ፣ በሁዋላ ድርጊት ውስጥ ስትገባ ለካ የምትጠቀመው ሁለት መስመር ብቻ ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ገላ (body) ያደክማል፡፡ እንደ ስንብት ቀለማት ዓይነት በጣም ረዥም ነገር ስትፍ፣ ዋናው ችግሩ የስሜትህ መለዋወጥ ነው፡፡ የደራሲው የግል ሙድ ወይም ጤና፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀርን ይበክላል፡፡ ከቀናህም ልዩ ይሆንልሃል፡፡ ይሄ ሁሉ ምቾት የለውም፡፡ ለአንተ የሚቀርህ የመንፈስ ደስታው፡፡ የመንፈስ ደስታ ደሞ የአንገት ስትራፖ አይፈውስም፡፡

የሽፋን ሥዕሉ ሐሳብ የማነው? የሰባት ሰው ገጾች - 4ቱ ወንዶች፣ 3ቱ ሴቶች፤ ስድስቱ ደግሞ ወደ መካከለኛዋ ሴት ዞረዋል…

ጽንሰ ሀሳቡ ከሠዓሊው ጋር የተመካከርንበት ነው፡፡ የሠራው ሥዕል ግን ልክ እኔ እንደፈለግኹት ነው፡፡ የፊት ለፊቱንና የኋላው ሽፋን ላይ ያለውን አንድ ላይ ነው ማየት ያለብህ፡፡ የፊት ለፊቱ የተዋረድ ሥልጣንና ማዕከል ያለው፣ ሥርዓት ያለው ፓተርን

ነው፡፡ የጀርባው ጥልቅ የኾነ የመረብ ግንኙነቶች ያሳያል፡፡ አንድ ጸሐፊ ሊሰራው የሚገባውን ነገር ያሳያል፤ ትልቅነትን፡፡ ሥርዋጽ፣ የኅዳግ ማስታወሻና አባሪ መግለጫ... በተለይ የኅዳግ ማስታወሻው ታሪኩን አቋርጦን ይሁን ወይም ተመልሰን የምናነበው ይቸግራል፡፡ እንዴት ይነበብ? - ምናልባትም፣ ይህንንም ሊመልስልን ይችላልና... እስኪ ስትጽፈው እንዴት እንደነበር ግለጽልን፡፡ አልፈህ ሄደህ እየተመለስክ ጻፍከው፣ ወይስ በያለበት ዋናውን እያቋረጥክ?

አንዳንድ የኅዳግ ማስታወሻዎች ተጨማሪ ትረካዎች ናቸው፣ አንዳንዶች የግል ሕይወት ታሪኮች፣ አንዳንዶቹ ታሪካዊ (ፍሑፎች) ናቸው፡፡ የኅዳግ ማስታወሻዎቹ በታሪክ ዘመን ቅደም ተከተል ስላልተደራጁ (አንባቢው) በተመቸው መንገድ ያንብበው፡፡

ትምህርተ ጥቅስ አለመጠቀምህ ይሁነኝ ብለህ ያደረግኸው ነው?

ትምህርተ ጥቅሶች ገጾችን እንዳሉ ይሞላሉ፤ ስለዚህ ሙተው መደነጋገርን ያስወግዳል፡፡ እንዲህ ማድረጉ አይቀልልም? ዋናው ነገር አንባቢ ተረድቶኛል ወይ? የሚለው ነው፡፡

እንጀራን መቸም አትለቀውም፣ አይደል?

የእንጀራን ታሪክ ልፃፍ ብል ከሁለት ገፅ የበለጠ አይሄድም፡፡ እሱን መፈለግና ማብራራት የምግብ አንትሮፖሎጂስቶች ስራ ነው፡፡ ከእንጀራ የምዋሰው ነገር ቢኖር፣ ለሕናዊነት ሕልውና ማስረጃ (ኦንቶሎጂካል እስታተስ) የሚጠቅሙኝን የልዋጭ ወይም ስነ-ትዕምርታዊ ሴማዮቲክ መደምደሚያዎችን ነው፡፡ የዚህ አይነት ነገር ስላልተሰራ በመጠኑ ራሴ መልፋት አለብኝ፡፡ ራሴ ስለፋ ደሞ ያልሰለጠንኩበት መስመር ስለሆነ የሆነ ነገር መግደፌ አይቀርም፡፡ እና በአጭሩ እንጀራ መሳሪያ እንጂ የአላማዬ የመጨረሻው ግብ አይደለም፡፡

የእንጀራ አመጣጥ ሁለት ተፎካካሪ በሃይማኖት ወይም በኅሳ መስመር የተከፋፈሉ ትረካዎች አሉት፡፡ አንደኛው ተደጋግሞ የሚነገረው ትረካ፣ ከብረነገስት ወስጥ የሰፈረው ነው፡፡ እዚህ ውስጥ ያለው ተረክ ብዙ የማይታመኑ ነገሮች ቢኖሩበትም ለስነሁፍ ይጠቅማል፡፡ ሁለተኛው የመሐፈ ሱባኤ ተረክ ነው፡፡ ይሄኛው ወደ እውነታ ይቀርባል፡፡ መነሻ ያደረኩትም ይሄንን ነው፡፡ ሁለቱም ጎኖች ልብ ወለድ ወስጥ ያስፈልጉሃል፡፡ ልብ ወለድ መፃፍ በሆነ መልክ መላምት ፍተሻ ነው (ሃይፖቴሲስ ቴስቲንግ)

ስንዝሮ በአፋዊ ትረካ የታወቀ ነው፡፡ ታሪክን ተራኪ ልታደርገው የመረጥክበት ምክንያት ምንድነው?

የስንዝሮ ታሪክ ሁላችንም ያደግንበት ታሪክ ነው፡፡ ማለት ሁላችንም በማወቅ የምንጋራው ተረት ነው፡፡ በመጀመሪያ፤አንደኛ ደረጃ ስማር አስቆኛል፡፡ አሁንም ያስቀኛል፡፡ ያን የድሮ ሳቄን ለማስታወስ፡፡ ሁለተኛ፤ በቅርብ ጊዜ ሳነብና ስሰማ ሰዎች እንደሚመቻቸው አድርገው ታሪክ ሲተረጉሙ ያጋጥመኛል፡፡ ይሄ አተረጓጎም ሙልጭ አድርጎ መካድ ድረስ ይሄዳል፡፡ በየቦታው ውሸት ማስገባት፣ ትርጉም እንዳሻ ማምጣት ወዘተ ያጋጥመኛል፡፡ እኔስ ቢያንስ ይሄ የማበላሸት ነፃነት ለምን ይቅርብኝ? ተጠየቅን ከማደፍረስ ጋር ልታያይዘው ትችላለህ፡፡ ሶስተኛ፣ ስንዝሮ በተረት ዓለም አቀፍ ሁለንተናዊ ባህርይ አለው፡፡ በሚቶሎጂ ትሪክስተር አርክታይፕ የሚባለው፡፡ በእንስሳት መስመር በሃገራችን ጦጢት (ሁልጊዜ እንስት ናት) አለች፡፡ በፈረንጆች ቶም ዘ ሰም(ብ) አለ፡፡ ይሄ የስንዝሮ ሁለንተናዊ ቦታ፣ ባህልህን በቀላሉ እንዲነጠቅ ያደርገዋል፡፡ ዛሬ የኤዞፕ ተረቶች ለላፎንቴን ተሰጥተዋል፡፡ በአንተና በተረቶቹ መሃል ፈረንሳዊ ሰውዬ ገብቷል፡፡ ተረቱን ወደ አገሩ የመመለስ ነው፡፡ አራተኛ፣ የስንዝሮን ተረት ሳነብ ብልጠቱ በራሱ ተወስኖ የሚቀር ነው፡፡ በትክክል የጀገነ አይደለም፡፡ ስለዚህ በነባር ተረቱ (በእንቅልፍ ለምኔ ላይ የተሰጠኝን ወስጄ) በመጠኑ ወደ ሰፋ ነገር ላመጣው ፈለኩ፡፡ ይሄም ባህርዩን መለወጥና ልዋጤውን የሰፋ ታሪካዊና ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ ለመክተት መሻት ነው፡፡

አምስተኛ፣ የስንብት ቀለማት ከተለያዩ የግለሰብ ታሪኮች የተሰራ አሴምብላጅ ኖቭል ነው፡፡ አሴምበላጅ የኤማኑኤል ደ ላንዳ ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡ ደ ላንዳ ስለ ዴሉዝ ትርናስደንታል ኤምፐሪሲዝም ማብራሪያ በመስጠት የታወቀ፣ ከዛም በመነሳት በራሱ ያዳበረውን አሴምብላጅ ቲዮሪ ወደ ስነ-ሰብ (ማህበራዊ ሳይንስ) ያመጣና ስለ አቀራረቡ አዲስነት ክርክር የከፈተ ሰው ነው፡፡

ምን ማለት ነው? ሙሉ የተባሉ ስርዓቶች (ሲስተምስ) ንዑስ ክፍሎች ቢኖራቸው በነዚህ ሁሉ መሃል ያለውን ግንኙነት ማለት ንዑስ ለንዑስ፣ ንዑስ ከስርዓት ጋር ያለውን ግንኙነት ማየት ነው፡፡ ይሄ ቲዮሪን ወደ ልብወለድ ስናመጣው አንድን ንዑስ (ፀባዩን) ካለበት ስርዓት አውጥተህ ሌላ ስርዓት ውስጥ ማስገባት እንደምትችል፣በዚህም ዋቤነቱ እንደማይበላሽ ማሳየት ነው፡፡ ለምሳሌ ሸራ ኳስ የግራውንድ ቴኒስ መጫወቻ ብትሆንም ከተሰራችለት አላማ ከሜዳው ውጭ ብናገኛት፣ አስፋልት ላይ ቴብል ቴኒስ ወይም ጢብ ጢብ እንጫወትባታለን፡፡ የግራውንድ ቴኒስ ስርዓት ወደ እግር ኳስ ስርዓት ወይም ከፍተኛ ገቢ ከሚጠይቅ ስፖርት ጨዋታ ወደ ሌላ ዝቅ ወዳለ ስርዓት ይሸጋገራል ማለት ነው፡፡ አሰምብላጅ ስጠቀም ጠቅላላ በራሱ አለም የተንፈላሰሰ የመሰለውን ድርሰት፣በመጠኑ የታሪክ ስርዓት ውስጥ ለመክተት የስንዝሮን ገፀባህርይ ተጠቅሜአለሁ፡፡ ነጠላ የመሰሉ ታሪኮችን ሰብስቦ የሚወስድ የሆነ ሃዲድ ያስፈልጋል፡፡ ያ መስመር ስንዝሮ ነው፡፡ የስንዝሮ መስተጋብር ከተወሰኑ ገፀባርያት ጋር ብቻ ስለሆነ መስመሩ ቀጭንና ሽክሽክ ነው፡፡

ስንዝሮን ግን ካለው ምልከታዊነት ጋር የግብፃውያንን አማልክት አማኝ አድርገኸዋል፡፡ ለምን ያንን ሰጠኸው? ኢትዮጵያውያኑም ለግብፃውያን ጣዖታት የተሰጡ ናቸው፡፡ ይህ ከአንድ አምላክ እምነት አማኝነታቸው ጋር ይቃረናል፡፡ ገጸባህርያቶችህም ያላግባብ አንድ አምላክ እምነትን ያንኳስሳሉ…

ምክንያቱ (ስንዝሮ) ገጸባህርይ ስለኾነ ነው፡፡ ሐሳቡ ቀጣይ ታሪክን መፍጠር ብቻ ነው፣ ጊዜ የለሽነትን የሚጠጋጋ፡፡ ስንዝሮ በአሞን ራ እና በሌሎች አማልክት መካከል ይመላለሳል፡፡ አንድ አምላክን ሌሎች አማልክትንም ያምናል፡፡ ጉዳዩ ግን ይህ አይደለም፡፡ (በነገራችን ላይ፣ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ በጥንታዊቱ ግብፅ አማልክት የሚያምኑ ሰዎች ነበሩ፣ ጊዜውን እርግጠኛ ባልኾንም፣ በ13ኛው ወይም በ14ኛው መቶ (ከልደት ወዲህ)፡፡ ንጉሥ ካሌብ ክርስቲያን ቢሆንም በውሻ ኮከብ ያምን ነበር፡፡ ራሱ ካሌብ የሚለው ስሙም ከልብ ወይም ውሻ ማለት ነው)…

በነገራችን ላይ፣ ስንዝሮ ኢዞጵን በጭራሽ አላገኘውም፡፡ ይሔ ልብወለድ ነው፡፡ ጉዳዩ በአጭርና በጠበበ መጠን የኢትዮጵያን ታሪክ ገጽ ማቅረብ ነው፡፡ ሃይማኖቱ ምንድን ነው የሚለው አያሳስበኝም፡፡

አንዳንድ ምንጮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ካሌብ የሚለው ከዐረብኛ ሊያገናኙት የሚሞክሩ ይኖራሉ፡፡ እንደ ጋስፓሪኒ ያሉ ታሪክ ፀሐፊዎች ሆን ብለው ማያያዝን ይመርጣሉ…

ከልብ ዐረብኛ ነው እንዴ? ጋስፓሪኖን አላነበብኩትም፡፡ በሌላ መጽሐፍ ነው ያነበብኩት፣ ስለ ውሻ ኮከብና ሌሎችም፡፡ ክርስቲያን ኾነው የቡድሂስት እምነት የደረቡ ነገሥታት ነበሩ፡፡ ምንጊዜም ቢሆን መለዋወጥ ነበረ፡፡ በሽግግሩ የነገሥታቱ አባላት ሌላ ሃይማኖት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ወዘተ… የኢትዮጵያ ንጉሥ ስሙን የሚያገኘው ከራሱ ቋንቋ ነው፡፡ ምናልባት ከልብም የአማርኛ ቃል ሊሆን ይችላል ወይም ሌላ የኢትዮጵያ ቋንቋ፡፡ እና እነዚያ የዚያን ጊዜ ሰዎች ሌሎች አማልክትን በማምለካቸውም ይኮሩ ነበር፡፡

የብዙ አማልክትም የአንድ አምላክ እምነትም አንድ ላይ የነበሩባቸው ዘመኖች ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ በአንዴ ክርስትያን ሆነ ብለህ ታስባለህ? ሌላው ቀርቶ ነገሥታቱና ቤተሰቦቻቸው? ለኔ ቁብ ያለው ነገር ኢትዮጵያዊ መሆኑ ነው፡፡ ስንዝሮ የጊዜ ተጓዥ ነው፡፡ (በየዘመኑ) ያየውን በአጭር ገጾች ይነግረናል፡፡

አንተ በግልህ ስለ ጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ ምን ይሰማሃል?

የታሪክ አዋቂ አይደለሁም፤የታሪክ ተማራማሪም አይደለሁም፡፡ የተለያየ ቦታ ያነበብኳቸውን የተበታተኑ መረጃዎች በመውሰድ፣ የወሰድኩትንም በመቀበል (ሪኮግናይዝ በማድረግ) ስሩን ሳላዛባ በልብወለድ ልጫወትባቸው እሞክራለሁ፡፡ ስማቸው የተጠራ የአገራችን የታሪክ አዋቂዎች ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ስለ ኢትየጵያ ታሪክ ሲፉ፣ ጉጉት እንኳን ገፍቷቸው ወደ ምዕራብ ዞር ብለው አባይን ተከትለው መመርመር አይደፍሩም፡፡ ትምህርት ቤት ከተሰጣቸው መስመር፣ ዲግሪ ካበረከተላቸው ተረክ የማይወጡ ናቸው፡፡ የስንዝሮ ታሪክ በልብወለድ የተቦካ ስለሆነ የሚረጋገጥ (ቬሪፋይድ) ዕውነት እጥረት ቢኖርም የመቼት አመራረጡ ሂስ አለበት፡፡

አዲሱ ልብወለድህ ምን ዓይነት ዘውግ ውስጥ ይመደባል? (ቴዎድሮስ ገብሬ ኤፒኮ ኖቭል ብሎታል)
ዣነር (ድካ) አያሳስበኝም፡፡ አንደኛ የዣነር ንሰ-ሃሳብ አውሮፓዊ መሰረት ያለው ነው፡፡ በአውሮፓ ሊተራሪ ታሪክ፣ ዣነሮች የተነሱበት የገነኑበት የወደቁበት ጊዜ ይጠናል፡፡ አህጉሩ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ አገር የየራሱን ተርጓሚ ይቀርፃል፡፡ እኛ እዚህ ውስጥ የሚያስገባን ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም የለም፡፡ ጦቢያ ልብወለድ ከመጀመሪያው ለምን ተፃፈች ብለህ መጠየቅ፣ ለመጠየቅ ካልሆነ መልሱን በትክክል ማወቅ አትችልም፡፡ ጦቢያን ያነበብከው ትረካ (ናራቲቭ) ስለምትወድ ብቻ ነው፡፡ መተረክ ባህልህ ውስጥ ነባር እሴት ነው፡፡ ስለዚህ ከትረካ ለምን አንጀምርም? ልብወለድ ውስጥ ድራማ አለ፣ ድራማ ወስጥ ግጥም አለ፤እያንዳንዱ ድካ ሌላ ውስጥ አለ፡፡ አንዱ በአንዱ ኤማነንት ነው፡፡ በእኔ ረኸፃም ልብወለድ ሁሉን ሊውጥ ይችላል፡፡ የመፃፉ ነገር እንጂ ድካ አያሳስበኝም፡፡ ከሁለት የተውሶ የግጥም መስመሮች ተነስተህ፣ በእነሱም ተነሳስተህ፣ በአካልም እነሱን እየጠራህ ልብወለድህን ካዋቀርክ፣ ልብወለዱ ምን ሊባል ነው? ዣነር ችግሩ ንፁህ ቅርፆች ፍለጋ መሄዱ ነው፡፡ ከግንኙነት ውጭ ንፁህ ራሳቸውን የቻሉ ሰዋዊ ነገሮች የሉም፡፡ ግንኙነት ንፁህ መሆንን ይከልሳል፡፡ ይሄን ክልስነቱን መቀበል አለብህ፡፡ ሕናዊነት ከገፀባህርይ ወደ ገፀባህርይ እንደሚዘለው ወይም ከኩነት ወደ ኩነት ወዘተ……ከድካ ወደ ድካ ይዘላል፡፡ በዚህም ሂደት ወደ ራሱ ውስጥ ይከታቸዋል፡፡

"ሀገር በዚህ ወጥቶ፣ በዚህ ገብቶ የሚል መጽሐፍ አልወድድም" ብለህ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ አዲሱ መጽሐፍህ "ንፋስ ስልክ" በተባለች ቦታ ስለተመሰለች ሀገር እየተናገርክ ነው--

ፖለቲካ አይደለም የምጽፈው፡፡ እኔ፤"ማንኛውን ነገር እየጻፍኩ ነው፤ወይም ለመጻፍ እሞክራለሁ፡፡ ታሪኮችን ስታነብባቸው ብዙ ዚግዛጎች ውስጥ ታልፋለህ፡፡

የተመሳቀሉ ርእሰ ጉዳዮች ይሰሙሃል፡፡ እዚህ ላይ ስፍራና ቦታ አለ፡፡ ጉዳዮች ስለተደረጉ ስለ ሀገር መናገርን ልታስወግደው አትችልም፡፡ በተለጠጠው የዓለም ተቋም ውስጥ የሚታይ ቦታ ይዞ የሚገኝ ስለሆነ (አታስቀረውም)፡፡
"በመንፈስም በሥጋም ግባችንን መሰናበት" የምትለው ጭብጡን የጠቀለለች አትሆንም? ከሆነች ከዋነኞቹ ባለታሪኮች ውጭ፣ አቶ ዮሐንስ ወላይሶ እንዲናገራት ለምን ተደረገ?

ዮሐንስ እኮ ባለታሪክ ነው፡፡ የእሱ ታሪክ እሚነገረው በሕዳግ ማስታወሻ ነው፡፡ ሐያሲ ነው፡፡ ሐያሲዎች አብዛኛውን ጊዜ ገለል ብለው የሚያዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ የግርጌ ማስታወሻው ገለልታውን ያሳያል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን በገዛ ራሱ ጽሑፎችም ኾነ ሌሎቹ ሰዎች ስለሱ በሚናገሩት ስለርሱም እናውቃለን፡፡ "ያገር ልጅ ዘውዘው" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ እና የሕዳግ ማስታወሻው የርሱ ሕይወትና ሒሶቹ (ወይም ስለሚያየው ነገር ያለው አተያይ) ብቻ አይደሉም፡፡

የአንድ መጽሐፍ ትልቅነት ራሱን የቻለ አንድ ነገር ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትላልቅ መጻሕፍት በየይነውዳቸው ተለይተው ይዘረዘራሉ፡፡ ከልብ ወለዶች በጣም ትልቁ እሱ ባይሆንም ባላቸው ደንብ መሰረት በጊነስ ቡክ የተመዘገበው የማርሴል ፕሮስት ልብ ወለድ ነው፡፡ ያንተ መጽሐፍ ከትላልቅ ልብ ወለዶች ውስጥ የቱ ጋ ሊሰፍር እንደሚችል እያየን ነው፡፡ ግን ያለውን የቋንቋና የመጻፍያ ምልክቶች ስርአት እንዲሁም የህትመት ግዶችንና ሌሎች ወሳኝ የሆኑ ነጥቦችን ሳናይ፤ከአፍሪካ ልብወለድ፣ ቁጥር ፩ ትልቁ መጽሐፍነቱ የማያጠያይቅ ሆኗል፡፡

እንደዚህ ከኾነ ቃላትን መቁጠር አለብኝ፡፡ በርግጥ ትልቁ ወይም በዓለም ደረጃ ላይ ነው የምንል ከኾነ ያን ማድረግ ግድ ይኾናል፡፡ ያ ደግሞ ጉረኝነት ነው፡፡ ከዚህ ዓይነቱ መወቀሻ ከሚኾን ጉዳይ እኔን አውጣኝ፡፡ ሃሃሃ--- በእርግጥ ያንን የሚያደርጉበት የተለያዩ መሥፈርቶች እንዳሉ ግን አውቃለሁ፡፡ እዚህ ላይ እንግሊዝኛንና አማርኛን ልታወዳድር ነው፡፡ አማርኛ ዋየሎች ስለሌሉት ከእንግሊዝኛው ያንሳል፡፡ ስለዚያም ነው ለተመሳሳይ ነገር ባነሱ ገጾች ላይ የጨረስኩት፡፡ የገጽ ብዛትንም መጠቀም አንችልም (ይመስለኛል)፡፡

ከእንግዲህ ግን ከ300 ገጽ የበለጠ መጽሐፍ አልጽፍም፡፡ ምክንያቱም 350 ብር መክፈላቸው የሚሰማቸው ይኖራሉ፡፡ መጽሓፉ ግን ከ1300 ገጽ በላይ ነበር፡፡ ጭምቅምቅ በማድረግ ነው በግማሹ ዋጋ የቀረበው፡፡ ይህን አስልቶ መረዳት ያልቻለ አንባቢ፤እኔንም አንብቦ ይረዳኛል ብዬ አላስብም፡፡ ቀላልና ግልጽ ስሌት ብቻ ነው፡፡--...

-ግን አንተ ፣መጽሐፉ ፖለቲካን የያዘ ነው ብለህ አሰብክ? እንዳለ ስለ አካሎች፣ ምግብ፣ ፍቅር፣ ኪሳራ፣ ወዘተ. ብቻ ነው፣ በቀልድና በቁም ነገር የቀረበው፡፡ ምናልባት፣ የግል ሕይወታቸው ወደ ፖለቲካው የገባባቸው ቢኖሩ፣የነርሱ ዕጣቸው ከፖለቲካዊ አጀንዳቸው የበለጠ ጉዳይ ሆኖ ነው የቀረበው፡፡ ከገጸ ባህርያቶቹ ሁሉ ምናልባት ዮሐንስና ቤላ በቀናት የፖለቲካ አዝማሚያ የሚታይባቸው ይመላለሳሉ፡፡ (ዮሐንስ ይበልጥ ወደ ባህሉ ነው) በማንበብ ሁሉንም ታገኘዋለህ፡፡

እንዲያውም አንድ ነገር አስታወስከኝ፡፡ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ጠንከር አድርገህ አለመያዝህን እየታዘብኩ ነው ያነበብኩት፡፡ በተለይ የዚህን ዘመን ሥርዓት የሚመለከተው ላይ ፈራ ተባ ያልክ ትመስላለህ፡፡ ፖለቲካ ትፈራለህ እንዴ?

በወቅታዊ ፖለቲካዎች ላይ ብዙ ብያለኹ እንዴ? በ1985/86/87 የኢትዮጵያ ዘመኖች ጥቂት ነገሮች አሉ፡፡ ያ ወቅታዊ አይደለም፡፡ ጶለቲካ ከሙብላት፣ ከመጠጣት፣ ከወሲብ፣ ከመዝፈን ፣ከመራመድ፣ ከመተንፈስ ፣ከእስክስታ፣ወዘተ.የተለየ ነገር አይደለም፡፡ እያንዳንዱን ምራፍ ብታይ የፖለቲካው ክፍል ትንሽ ነው፤የሌሎች ጉዳዮች ኦርኬስትራ አካል ብቻ ነው፡፡ ፍቅር ማሲንቆ ከኾነ፣ሀገር መውደድ (አርበኝነት) ክራር ከኾነ፣የሰው ገላዎች ደናሾች ከኾኑ፣ወዘተ---በኔ እምነት፣የስንብት ቀለማት የተለያዩ ጉዳዮች የተውሰበሰቡበት ነው፡፡ ምንም ነገር ገንኖ አልወጣም፤ምንም ነገር ኮስሶ አልቀረበም፡፡ ልክ በ80ዎቹ እኩሌታ ላይ በነበረችው ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳለህ ይሰማሃል፡፡ ኹሉንም በምልዓት ታገኘዋለህ፡፡

ልጆችህ አማርኛ አይችሉም፡፡ ድርሰትህን ባለማንበባቸው ቅር ይልሃል?

የሚፈልጉ ቢሆን ቅር ይለኝ ይሆናል፡፡ እስከ አሁን አልፈለጉም፡፡